በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ሚኒስቴር

ብሔራዊ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ሚኒስቴር

የብሔራዊ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የብሔራዊ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የብሔራዊ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 980/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዓለም አቀፍ ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው።

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፣ አጥጋቢ ማረጋገጫና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ

አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ይሁን የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት የብሔራዊ ደምና ቲሹ አገልግሎቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ወስዶ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት በብሔራዊ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የተዘጋጁ የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣
- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የብሔራዊ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በቀድሞው የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

1. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

<u>ንብረት አስተዳደር</u>

1.1 የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል አራት አንቀጽ 09 ንዑስ አንቀጽ1 (ሀ-መ) በተመለከተው መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተሰብስበው ስልጣን በተሰጠው በመንግስት አካል መወገድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 05 ንኡስ አንቀጽ 2 የአላቂ እና የቋሚ ንብረት ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር መመዛዘን እዳለበት ይገልጻል፡- መመሪያ በሚያዘው መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተሰብስበው ስልጣን በተሰጠው በመንግስት አካል መወገዳቸውን እንዲሁም የንብረት ቆጠራ እና ማመዛዘኛ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በመ/ቤቱ፡-

- 2014 በጀት ዓመት የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከወጪ ቀሪ ያልተመዛዘነ መሆኑ፤
- ንብረቶች የእሰቶክ መዝገብ ከወጪ ቀሪ ባላንስ (ሚዛን) እና የቢን ካርድ ከወጪ ቀሪ (ሚዛን) ያልታሰራ መሆኑ፤
- በአካላዊ ምልከታ በንብረት ክፍል ውስጥ ንብረቶቹ አዲስና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛታቸው 18 የሆኑ ቋሚ እቃዎች እና 10 የሆኑ አላቂ ዕቃዎች ተገዝተው መጋዘን መቼ እንደገቡ የማይታወቁ ምንም ሠነድ ሊቀርብላቸው ያልተቻለ መሆኑ፤
- በቋሚ ንብረቶች ላይ የንብረት ቁጥር (ታግ) ያልተለጠፈ መሆኑ፤
- በቀይ መስቀል ለቢሮ አገልግሎት በሚል በተከራዩት ህንጻ በአንደኛ ወለልና በምድር ቤት በሚገኙ ቢሮዎች ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡና በከፊል ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የተለያዩ የንብረቶች የሚገኙ ቢሆንም ዝርዝራቸው ቢጠየቅ ሊቀርብ አለመቻሉ፤
- በቋሚም፣ በአላቂ ዕቃዎች እና በህክምና እቃ ግምጃ ቤት በመመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 10 (ሀ) መሰረት የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት እንደሌለበት የተመለከተ

ቢሆንም የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ ሥራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤

- በርካታ በስጦታና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች ተከማችተው የሚገኙ ቢሆንም በንብረት ገማች ኮሚቴ ዋጋ የተሰጣቸው ቢሆንም እስከ ኦዲቱ መጨረሻ መወገዳቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ፤
- በመ/ቤቱ ምድር ቤት በሚገኘው የተሸከርካሪዎች ማቆሚያ ስፍራ በተሰራ የፓርተሽን ክፍል ተቆልፎበት በሚገኝ በርካታ የስፖርት ቋሚ ዕቃዎች የጤና ሚ/ር ንብረት ነው ከማለት ያለፈ ማስረጃ ቢጠየቅ ለቀርብ አለመቻሉ፤
- ብዛታቸው ሁለት የሆኑ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ባለቤትነት ደብተር (ሊብሬ) ላይ የተመዘገበው የሞተር ቁጥር እና በተሽከርካሪው ሞተር ላይ የሚገኘው ቁጥር የተለያየ መሆኑ፤
- በአካል ምልከታ ባደረግንበት ወቅት መ/ቤቱ በቀይ መስቀል ግቢ ውስጥ የተከራየው ጂ+1 ህንጻ ከምድር ቤት ከሚገኘው ሁለት ክፍሎች አገልግሎት ከመስጠት በስተቀር በመጀመሪያው ወለል ላይ የሚገኙት ክፍሎችና ከምድር ቤት ያሉትን የቢሮ አገልግሎት መስጠት የሚገባቸው ክፍሎች፤ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ማከማቻ በማድረግ የወጪ ቁጠባን ዘዴ መፈለግ ሲገባ ለዓመታት ለቢሮ አገልግሎት ሳይውል ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ እንዲሆን መደረጉ፤
- በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ 1164/10 በክፍል ሁለት በንኡስ አንቀጽ 5 ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ደረጃቸው ያልተወሰነላቸው አዲስ የስራ መደቦችን የስራ ዝርዝር አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ በማቅረብ ደረጃዎችን ያስወስናል በሚለው አዋጅ መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ መ/ቤቱ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውና በርካታ ንብረቶች እያስተዳደረ በመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች አደረጃጀት የንብረት ክፍል ለማን ዳሬክቶሬት ተጠሪ እንደሆነ ከመ/ቤቱ መዋቅር ያልተካተተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1.2 ባለፉት በጀት ዓመታት የሂሳብና የንብረት የኦዲት ግኝቶች

1.2.1 የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- በአገልግሎቱ መ/ቤቱ ውስጥ የሚሰሩ በቁጥር 20 ሾፌሮች እና የጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ ለሆኑ ሠራተኛ የእራት አበል በማለት ብር 118,566.00 ክፍያ ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ መሆኑ፤

1.2.2 የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- በውሉ መሰረት ሲስተር ዳግማዊት ፋንታሁን ከህዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ አንድ ዓመት ከስምንት ወር ሙሉ ደመወዝ እየተከፈላቸው በትምህርት ላይ የቆዩ ሲሆን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ለ3 ዓመት ከ4 ወር ማገልገል ሲገባቸው ለ10 ወር ከ14 ቀን ብቻ ሥራ ላይ ቆይተው ከነሐሴ 1 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ በማቆማቸው በውሉ መሰረት መ/ቤቱ ካወጣው ወጪ ውስጥ ግለሰቧ ወይም ዋሶቻቸው ብር 54,754.00 እንዲከፍሉ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 132,974.00 ያልተመለሰ መሆኑ፤

1.2.3 የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- ለሁለት ሰራተኞች ያለደመወዝ የዓመት ፍቃድ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው በተፈቀደላቸው መሰረት ያለ ደመወዝ የወሰዱት እረፍት ታስቦ ከወር ደመወዝ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ ሲገባ አለአግባብ ከተከፈላቸው የተጣራ ደመወዛቸው ብር 1,054.20 ውስጥ ብር 941.73 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 112.47 የተጣራ ተከፋይ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- አራት ሰራተኞች መሥሪያ ቤቱን ከለቀቁ በኋላ የተፈጸመው የተጣራ ተከፋይ ብር 11,070.13 ተመላሽ እንዲደረግ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ብር 2,286.30 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 8,783.83 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

1.2.4 የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- በመሥሪያ ቤቱ በደብረታቦር ከተማ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ከተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋር ከሰኔ 10 እስከ ሰኔ 12 ቀን 2008 ዓ. ም ድረስ ባካሔደው የምክክር ጉባኤ ላይ ለተካፈሉ

ተሳታፊዎች ለመኝታ ብር 40,688.16 ለምሳና ለእራት አገልግሎት ብር 37,557.12 በድምሩ ብር 78,245.28 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ለመሂጃና ለመመለሻው ብቻ የ3 ቀን የውሎ አበል በጠቅላላው ብር 31,728.00 መከፈል ሲገባው ለእያንዳንዳቸው የ8 ቀን ውሎ አበል በጠቅላላው ብር 85,690.00 በመከፈሉ ምክንያት ከመመሪያው ውጪ የ5 ቀን የውሎ አበል ብር 53,962.00 አለአግባብ ክፍያ መፈጸሙ ተገልጾ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ከደም ባንክ አገልግሎቱ ሠራተኞች ላይ ብር 9,459.00 ተመላሽ የተደረገ ቢሆንም ብር 44,503.00 ግን ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

ከላይ የተገለጹት የባለፉት አመታት ግኝቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግባቸው አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ የመውሰዱ ሂደት መጓተት የሚታይበት መሆኑ ታውቋል፡፡

2. <u>የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Issues)</u>

2.1 <u>ከሚመለከተው ኤጀንሲ ፈቃድ ሳያገኝ የተፈጸመ ግዥን በተመለከተ</u>፤

የመድኃኒት ፈንድ እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ ለማቋቋም በወጣ አዋጅ 553/1999 አንቀጽ 15/2 መንግስታዊ የጤና ተቋማት በሙሉ የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት ፍላጎታቸውን በቀጥታ ለኤጀንሲው ብቻ ጥያቄ በማቅረብ ይገለገላሉ ይላል፡፡ ኤጀንሲው የተጠቀሱትን መድኃኒቶች ለማቅረብ በማይችልበት ወቅት ለጠያቂዎች ተገቢውን አማራጭ መፍትሔ እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡ መመሪያዉን መሰረት በማድረግ የአገልግሎቱን የመድህኒት ግዥ ሂደት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ተቋሙ የተለያዩ መድህኒቶች በድምሩ ብር 1,699,565.00 ግዥ ሲፈጸም ከመድኃኒት ፈንድ እና የመድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ መድህኒቶቹ አለመኖራቸዉን የሚገልጽ (Stock out) ማስረጃ ሳይቀርብ ከሌሎች የግል መድኃኒት አቅራቢዎች ግዥ የፈጸመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

2.2 <u>ከወጪ ቅነሳ መመሪያ ውጪ የተፈጸመ ግዥ በተመለከተ</u>፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በቁጥር ጠ47/41/6/6 በቀን 19/11/2009 ግንቦት 25 ቀን 2009 ዓ.ም የፌደራል መንግስትን የወጪ ቅነሳ

ተግባራዊነቱ እንዲቀጥል በቁጥር ጠ1/6/2 በቀን 18/02/2011 በተላለፈው ደብዳቤ በመመሪያ ተራ ቁጥር 7 በመ/ቤቱ የሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በሚያከናዉንበት ወቅት በአግባቡ በመፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን በመቀነስ ግዥ ማከናወን እንደሚገባ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ወርክሾፖች እና ሴሚናሮች እንደ ሻይ፣ ቡና እና ውኃ ከመሳሰሉት ወጪዎች በስተቀር ሌላ ግብዣ ማድረግ አይቻልም፡፡በመሆኑም አገልግሎቱ ከላይ በተገለፀው መሰረት ማከናወኑን ለማረጋገጥ በናሙና የተመረጡት ሰነዶችን ኦዲት ስናደርግ በቀን 13/102014 በቫውቸር ቁጥር 0005745 ብር 131,997.00 ወጪ በማድረግ በቁጥር 600 ቲሸርት ከዲ.ኤ.ኤፍ ማተሚያ መመሪያው ከሚያዘው ውጭ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.3 <u>የቀጥታ ግዥ በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 በወጣው ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት፣ የፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዢ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ይላል፡፡

በዚህም መሠረት የአገልግሎቱ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከአንድ አቅራቢ ቤት በመከራየት የአንድ ዓመት የቤት ኪራይ ብር 6,692,927.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
- የደም መለገሻ አልጋ በብር 234,000.00 ግዢ መፈጸሙ፤

➢ የማስታወቂያግዥ ከ5 ከተለያዩ የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች በብር 2,599,059.98 በድምሩ በብር 9,525,986.98 በመመሪያው መሰረት ከግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ውጪ ሌላ የግዥ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ለምን በዚህ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንደመረጡ ምንም ማስረጃ ሳያስደግፉ እና የወቅቱን የገበያ ዋጋ ጥናት ተደርጎ በጥናቱ መሰረት የተሻለ ዋጋ ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ ሳያያይዙ ያለውድድር በቀጥታ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.4 የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥርን በተመለከተ፤

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፤ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት በተላለፈው መመሪያ መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ጠቅላላ ድምር ብር 419,510.00 ከሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ፍቃድ ሳያገኝ ለኮንትራት ሠራተኛ ደመወዝ ወጪ ሆኖ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.5 ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ፤

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር

4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፣ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በደም ባንክ አገልግሎቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትል ባለመደረጉ ምክንያት በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ በሂሳብ መደብ 5217205 ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 51,595.78 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5217306 ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 6,601.75 በድምሩ ብር 58,197.53 በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የሚታይ መሆኑ፣

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

ጥር 2015 ዓ.ም